የሠበር መ/ቁ. 24153

መጋቢት 26/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” አብዱልቃድር መሐመድ

” አሰግድ ጋሻው

” መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ሪት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- አቶ መንግሥቱ አባተ

ተጠሪ፡- የባህርና ትራንዚት ድርጅት

*የስራ ክርክር - የስራ ውል መቋረጥ - ያለማስጠንቀቂያ ከስራ መሰናበት -አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ተ)*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበተው በህጋዊ መንገድ ነው ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

ሀሰተኛ የተባለ የትምህርት ማስረጃ ቀርቦ አልታየም፣ የቅጥር ፎርም ላይ ተጠቀሰ የተባለ በእኔ የተሞላ አይደለም የሚለው ክርክር የማስረጃ ጥያቄ እንጂ መሠረታዊ የህግ ክርክር አይደለም፡፡



የሠበር መ/ቁ. 24153

መጋቢት 26/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ” አብዱልቃድር መሐመድ

3. ” አሰግድ ጋሻው

4. ” መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- አቶ መንግሥቱ አባተ ቀረበ

መልስ ሰጪ፡- የባህርና ትራንዚት ድርጅት የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

አመልካች የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19788 በ14/4/98 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔና የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 43690 በ21/7/98 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ሲል ግንቦት 24/98 ዓ.ም የተፃፈ የተሻሻለ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ለመ/ሰጪ ደርሶ የካቲት 1/98 ዓ.ም የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው አመልካች ለቅጥር ያቀረበው የትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑ ስለተረጋገጠ በሕ/ስምምነቱም ሆነ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ተ) መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ መሠናበቱ በአግባቡ ነው ተብሎ ውሣኔ በመሰጠቱ ነው፡፡

አመልካች በአቀረበው አቤቱታም ሀሰተኛ የተባለው የትምህርት ማስረጃ ቀርቦ አልታየም፣ የቅጥር ፎርሙ ላይ ተጠቀሰ የተባለውም በእኔ የተሞላ አይደለም የሚለው ክርክር የማስረጃ ጥያቄን የሚመለከት እንጂ መሠረታዊ የሕግ ክርክር ያለው ሆኖ ባለመገኘቱ በፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19788 በ14/4/98 የተሰጠው ውሣኔም ሆነ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43690 በ21/7/98 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡ ግራ ቀኙ ኪሣራቸውን ለየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡